Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 1 ፤ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም.

በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞች የሚሰራጭ

## በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የዩሮጋይኒኮሎጂ ስልጠና በሐምሊን



### በውስጥ ገፆች


| | |
|---|---|
| ዩሮጋይኒኮሎጂ ስልጠና | 2 |
| ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ | 3 |
| የስራ ደረጃና ደመወዝ ማሻሻያ ጥናት | 3 |
| የመረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ ስርዓት | 4 |
| 7ኛው ዙር የኮሌጅ ምርቃት | 5 |
| መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች | 6 |
| የማህፀን መውጣት ህክምና ዘመቻ | 7 |

## በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የዩሮጋይኒኮሎጂ ስልጠና በሐምሊን

ሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የዩሮጋይኒኮሎጂ ስፔሻሊቲ ስልጠናን ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሌኒየም የህክምና ትምህርት ቤት፣ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ እና ከአለም አቀፍ የፌስቱላ ፋውንዴሽን ጋር በጋራ በመሆን እየሰጠ ይገኛል፡፡



በመላው አፍሪካ በዘርፉ ጠንካራ የትምህርት፣ የህክምና እንዲሁም የጥናትና ምርምር ማዕከል መፍጠርን ራዕዩ ያደረገው የስልጠና ፕሮግራሙ አስቀድመው በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸው ሃኪሞችን ተቀብሎ ለሶስት ዓመታት በማሰልጠን ከተለመደው ወጣ ያሉና ውስብስብ ችግሮችን የማከም አቅምን በመፍጠር በዘርፉ እንደሃገር የሚታየውን የባለሙያ እጥረት እንደሚቀርፍ የስልጠና ፕሮገራሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ሬናታ ገልፀዋል፡፡

የሐምሊን ህክምናው ዘርፍ ዳይሬክተር እና ከመጀመሪያዎቹ ሰልጣኞች አንዱ የሆኑት ዶ/ር ፈቃደ አየናቸው በበኩላቸው ስልጠናው ቀደም ሲል የውጭ ሀገር ሙያተኞችን ድጋፍ እንጠይቅባቸው የነበሩ ውስብስብ ችግሮችን እራሳችን ማከም እንድንችል ከማስቻሉም በላይ የሐምሊን የክልል ቅርንጫፍ ሐኪሞችም ከተለመደው መደበኛ ቀዶ ህክምና የተለዩ ችግሮችን ባሉበት ቅርንጫፍ መፍታት ስለሚችሉ ዋናው ሆስፒታል ላይ የሚታየውን ጫና ይቀንሰዋል ብለዋል፡፡ በቅርቡ በባህርዳር የተካሄደው ውጤታማ የማህፀን መውጣት ቀዶ ህክምናም የዚሁ ስልጠና ፕሮግራም አካል መሆኑን ዶ/ር ፈቃደ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ዶ/ር ፈቃደን ጨምሮ ዶ/ር የሺነህ ከዋናው ሆስፒታል ፣ዶ/ር መላኩ ከመቀሌ፣ ዶ/ር ቢተው ከባህርዳር በሐምሊን በኩል ስልጠናውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡



## ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል



ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (ከ2010 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም) የሚተገብረውን ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ሲሆን በዝግጅቱም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ሠራተኞች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ “አሳታፊ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት እያደረግን ነው፡፡ በጋራ የምንተገብረው ስለሆነ በጋራ ማቀዱ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው፣” በማለት የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ ተናግረዋል፡፡

የዕቅዱን ዝግጅትም አዲስ ኮንቲኔንታል የጤና አጠባበቅ ኢንቲትዩት (Addis Continental Institute of Public Health) በዋናነት እያማከረ እንደሆነና የዕቅዱ የመጀመሪያው ረቂቅ በዚህ ወር መጨረሻ ተጠናቆ ለውይይት እንደሚቀርብ የዕቅድና ፕሮግራም ኃላፊ ዶ/ር ደምሰው በየነ ገልፀዋል፡፡

## አዲስ የስራ ደረጃና የደመወዝ ማሻሻያ ጥናት እየተካሄደ ነው

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ አዲስ የስራ ደረጃና የደመወዝ ማሻሻያ ጥናት ኖሎት በተባለ ድርጅት እያስጠና ነው፡፡

የሐምሊን የሰው ሃይል አስተዳደር ኃላፊ አቶ ተስፋዬ አባይነህ እንዳሉት አጥኚውን አካል የመምረጡ ሂደት ከጅምሩ ግልፅና ከተፅዕኖ በፀዳ ሁኔታ እንዲካሄድ በማሰብ ከድርጅታችን የተለያዩ የስራ ዘርፎች የተውጣጡ 9 አባላት ያሉት ኮሚቴ ተዋቅሮ ሂደቱን በበላይነት እንዲመራ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ኮሚቴው ስራውን ለማሰራት በወጣው ግልጽ ጨረታ አማካኝነት ካመለከቱ 5 ድርጅቶች አሸናፊውን ለመለየት በቅድሚያ ዝርዝር የመለያ መስፈርት አዘጋጅቶ በመመልመል ለመደበኛው የጨረታ ኮሚቴ መርቶ አሸናፊው ተለይቷል፡፡ አቶ ተስፋዬ አክለውም ኮሚቴው ከማስረጃዎች ባለፈ ተወዳዳሪዎችን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝቶ ብቃታቸውን የመፈተሽ ስራ ሰርቷል ብለዋል፡፡

በዚህ ጠንካራ የምልመላ ሂደት አልፎ ስራውን የተረከበው ኖሎት የተባለው ድርጅትም ለውድድር ባስገባው ሰነድ መሰረት በዘርፉ የካበተ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን ወደ ሐምሊን ልኮ ስራውን ካሳለፍነው መጋቢት ወር አንስቶ በይፋ ጀምሯል፡፡

ጥናቱን በቅርበት እንዲከታተል የተመረጠው ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ወ/ሮ በለጥሻቸው በበኩላቸው የስራውን በገለልተኛነት መከናወን ለማረጋገጥ ኖሎት ጥናቱን ያለምንም የአስተዳደር አካላት ጣልቃገብነት ሰርቶ ሲያጠናቅቅ ውጤቱን ለቦርዱ ውሳኔ እራሱ ያቀርባል፤ የማኔጅመንቱ ድርሻ የቦርዱን ውሳኔ ማስተግበር ብቻ ይሆናል ብለዋል፡፡ ሰብሳቢዋ በመጨረሻም ውጤቱ ሁሉንም ሰራተኛ ሊያስደስት ይችላል ባይባልም ከጅምሩ አንስቶ በሚደረገው ከተፅዕኖ የነፃ ክትትል ፍትሃዊ እንዲሆን ኮሚቴው አቅሙን አሟጦ ይሰራል ብለዋል፡፡

ጥናቱ በቀጣይ 3 ወራት ተጠናቆ ለውሳኔ እንደሚቀርብ ይጠበቃል፡፡

# ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ DHIS 2 (District Health Information System 2) ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ

- አጠቃቀሙን አስመልክቶም ለሰራተኞች ስልጠና እየተሰጠ ነው



ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የፕሮግራሞቹን መረጃ አያያዝ፣ አተናተንና አጠቃቀም የተሻለ ለማድረግ የሚያስችለውን DHIS 2 ( District Health Information System 2) የተባለውን ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ። አጠቃቀሙን አስመልክቶም ከ20 ለሚበልጡ ከክልል ሐምሊን ማዕከላት፣ ከዋናው መስሪያ ቤት፣ ከኮሌጅና ከደስታ መንደር ለተውጣጡ የስራ ክፍል ኃላፊዎች የአንድ ሳምንት ስልጠና ባሳለፊነው መጋቢት ወር በዋናው መስሪያ ቤት ተሰቷል።

የክትትልና ግምገማ ባለሙያ አቶ ሀብታሙ አጥናፉ እንደተናገሩት ይህ አይነቱ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የድርጅቱን የመረጃ አያያዝ ዘመናዊና ቀልጣፋ ከማድረጉም ባሻገር መረጃን በአንድ ማዕከል ለማደራጀት ያስችላል።

የዕቀቅድና ፕሮግራም ክፍል ኃላፊ ዶ/ር ደምሰው በየነ በበኩላቸው ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መዘርጋቱ ድርጅቱን በእጅጉ የሚያግዝ ከመሆኑም ባሻገር ነባርና አዳዲስ ለጋሾችን ቀልብ ለመሳብ የሚረዳ ነው ብለዋል።

DHIS 2 በሚል ስያሜ የሚጠራው ይህ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በድርጅታችን እንዲዘረጋ USAID በ Pathfinder Ethiopia ቢሮ በኩል ድጋፍ ያደረገ ሲሆን ስልጠናውን MSH የተሰኘ አለም አቀፍ ድርጅት አመቻችቷል።



> ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መዘርጋቱ ድርጅቱን በእጅጉ የሚያግዝ ከመሆኑም ባሻገር ነባርና አዳዲስ ለጋሾችን ቀልብ ለመሳብ ይረዳል ።
>
> *ዶ/ር ደምሰው በየነ*

## 7ኛው ዙር የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ምርቃት በሐምሌ ወር ሊካሄድ ነው



ሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ደረጃውን በጠበቀ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓቱ ለ7 ኛ ዙር ያሰለጠናቸውን 20 ተማሪዎች በሐምሌ ወር ሊያስመርቅ ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡ “የአገርቱን መደበኛ የትምህርት ስርዓት የጊዜ ሰሌዳ ለመከተልና የተመራቂዎችን ምደባ ከመንግስት የበጀት ዓመት ጋር ለማጣጣም ሲባል የምርቃት ስነ-ስርዓቱን እስከ አሁን በኮሌጁ ከተለመደው ጥቅምት ወር ወደ ሐምሌ ወር ማምጣት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፣” በማለት የኮሌጁ ዲን አቶ ዘላለም በለጠ ተናግረዋል፡፡

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በመከላከል ፕሮግራሙ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው በሙያ ክህሎታቸው የላቁ ሚድዋይፎችን በመጀመሪያ ድግሪ አሰልጥኖ መመደብ ሲሆን ኮሌጁ ከተቋቋመበት እ.አ.አ. ከ2007 ጀምሮ 105 ሚደዋይፎችን አሰልጥኖ በመላው አገርቱ ገጠራማ ክፍል በሚገኙ 36 የመንግስት ጤና ጣቢያዎች መድቦ በማሰራት ላይ ይገኛል፡፡

እጩ ተመራቂዎቹ በአሁኑ ወቅት ለሁለት ወራት የስራ ላይ ልምምድና የመመረቂያ ጽሁፍ ዝግጅት በየመጡበት አካባቢ ባሉ የመንግስት ጤና ጣቢያዎች ተሰማርተው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### አጭር መረጃ

- ከ1999 ዓ.ም እስከ አሁን ከኮሌጁ 105 ሚድዋይፎች ተመርቀዋል፡፡
- በመላ አገርቱ 36 በሐምሊን የሚታገዙና የሐምሊን ሚድዋይፎች የተመደቡባቸው የመንግስት ጤና ጣቢያዎች አሉ፡፡
- የሐምሊን ሚድዋይፎች በመደበኛ ስራቸው ከ50 ሺ በላይ እናቶችን አዋልደዋል፡፡
- በ36ቱ ጤና ጣቢያዎች የሐምሊን ሚድዋይፎች ከተመደቡ በኋላ በወሊድና ወሊድ ተያያዥ ምክንያቶች የሚሞቱ የእናቶች ቁጥር በእጅጉ ቀንሷል፡፡


## በተሻሻሉና አዲስ በተዘጋጁ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች ላይ ስልጠናዎች ለሠራተኞች እየተሰጡ ናቸው

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በተሻሻሉና አዲስ በተዘጋጁ የድርጅቱ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች ላይ በየደረጃው ላሉ ሠራተኞቹ ስልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል። ስልጠናዎቹ ሠራተኞቹን ከመመሪያዎቹና ከአሠራር ማኑዋሎቹ ጋር ከማስተዋወቅ ባሻገር የሠራተኞቹን በድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠትና የትግበራ ክትትል አቅም ለማሳደግ ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብሎም ይጠበቃል።

ተመሳሳይ ስልጠናዎች ወደፊት በተከታታይነት እንደሚሰጡ የገለጹት የድርጅቱ ኦፕሬሽንስ ማናጄር አቶ ጥላሁን ሞላ መመሪያዎቹንና የአሠራር ማኑዋሎቹን ተግባራዊ በማድርግ የአሠራር ክፍተት እንዳይፈጠር ሁሉም ሠራተኞች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። የፋይናንስ ማናጀር አቶ አስፋው ንጉሤ በበኩላቸው ስልጠናዎቹ በየደረጃው ለሁሉም ሠራተኞች መሰጠት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የተሻለ ድርጅታዊ የአሠራር ስርዓት ለመዘርጋት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ሊኖሩና ሊተገበሩ የሚገቡ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች ናቸው በማለት አስተያየታቸውን የገለጹት የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እንደአስፈላጊነቱ ወደፊትም የሚሻሻሉና አዲስ የሚዘጋጁ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስረድተዋል። እየተሰጡ ባሉትና ሊሰጡ በታቀዱት ስልጠናዎችም ሠራተኞች በሙሉ ፍላጎት እንዲሳተፉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

| የተሻሻሉና አዲስ የተዘጋጁ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች | |
|---|---|
| የተሻሻሉ | አዲስ የተዘጋጁ |
| የትምህርት ዕድገት ፖሊስ | የውስጥ ኦዲት ቻርተር |
| የሰው ሃይል ማኑዋል | የንብረት ገቢና ወጪ አደራረግ ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ስርዓት መመሪያ |
| የፋይናስ ማኑዋል | የኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ |
| የግዢ ማኑዋል | የኢሜይል ኮሚዩኒኬሽን መመሪያ |



## ሌላኛው የሐምሊን አስተዋፅኦ ለአጠቃላይ የሀገሪቱ እናቶች ጤና መሻሻል በባህርዳር...

የወሊድ ፊስቱላን ከመላ ሃገሪቱ ማጥፋት የሃገሪቱ መንግስት ፍላጎት ከመሆኑም በላይ ከምናከብራት እናታችን ዶ/ር ካትሪን በአካል የተቀበልነው አደራም ጭምር በመሆኑ ለማሳካት መትጋታችን ይቀጥላል፡፡ ይህ ከተልዕኮአችን አኳያ ሲታይ ግን አንዱ እንጂ ሁሉም አይደለም፡፡በህክምናው ዘርፍ ብቻ ከቀላል እስከ ከባድ የወሊድ ፊስቱላ ጉዳቶችን ከማከም ባሻገር በቅርቡ በድርጅታችን በተካሄደ ጥናት ውጤት መሰረት በሃገሪቱ በስፋት ቢታይም በበቂ ሁኔታ ያልታከመውን ሌላኛውን የወሊድ ጉዳት የማህፀን መውጣት ችግርን ባለን የካበተ ልምድ መሰረት በጥራት ለማከም አቅደን መስራት ጀምረናል፡፡

ከችግሩ ስፋት አኳያ በለቀማ ከማከም ይልቅ አስቀድሞ በታቀደ መልኩ ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ በዘመቻ መልክ ማካሄድ ቅድሚያ ተሰጥቶታል፡፡ በዚሁ መሰረት ባሳለፍነው ጥር ወር ከዋናው ሆስፒታል፣ከመቀሌና ከባህርዳር የሐምሊን ማዕከላት የተውጣጣ የህክምና ቡድን ወደ ባህርዳር ተንቀሳቅሶ ውጤታማ ስራን ሰርቶ ተመልሷል፡፡ ቡድኑ በዘመቻው 40 የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸው እናቶችን ለማከም አቅዶ ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ከምስራቅ ጎጃምና ደቡብ ጎንደር ዞኖች የመጡ 39 ታካሚዎች በባህርዳር ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል አይቶ ለቀዶጥገና ብቁ ለሆኑት 35 ታካሚዎች ሐምሊን የሚታወቅበትን ጥራት ያለው፣ ዘመናዊ መንገድን የተከተለና ውጤታማ ቀዶጥገና ማድረግ ችሏል፡፡

የሐምሊን ሜዲካል ዳይሬክተርና የህክምና ቡድኑ መሪ ዶ/ር ፊቃደ አየናቸው እንዳሉት የማህፀን መውጣት ችግር ልክ እንደ ወሊድ ፊስቱላ ጉዳት ሁሉ በታካሚዎቹ ላይ ተመሳሳይ የማህበራዊና ስነልቦናዊ ቀውስ የሚያስከትል የእናቶች ጤና ችግር በመሆኑ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከሐምሊን በላይ የካበተ ልምድን ከተሟላ የህክምና ቁሳቁስ ጋር አጣምሮ የያዘ ተቋም የለም፡፡ ከስትራቴጂ አኳያም ቢሆን ሐምሊን በወሊድ ሳቢያ በሚደርሱ ጉዳቶች ላይ ለመስራት የተቋቋመ እንደመሆኑ የማህፀን መውጣት ችግርን ማከሙ ስትራቴጂካዊ ስኬትን የሚያስገኝ ነው በማለት ዶ/ር ፊቃደ አክለዋል፡፡ ተመሳሳይ ዘመቻ በሚያዚያ ወር በደቡብ ክልል ይርጋለም እንደሚካሄድ ከሜዲካል ዳይሬክተሩ ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

የባህርዳር ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል ዋና ሃኪም እና የማዕከሉ ኃላፊ ዶ/ር ቢተው አበበ በበኩላቸው ዘመቻው በክልሉ በመካሄዱ የክልሉ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ያስደሰተ ከመሆኑም በላይ በቀጣይ ከሐምሊን ጋር በቅርበት ለመስራት ቃል የገቡ በመሆኑ ድርጅታችን በመንግስት ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ያሳድገዋል፡፡ የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዘመቻው በክልሉ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ላደረገው ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ምስጋናቸውን በዶ/ር ቢተው አማካኝነት አድርሰዋል፡፡ በዘመቻው ሴቶቹን ለዘመናት ከኖሩበት የተነጠለ ህይወት ማላቀቅ ከመቻሉም በላይ የክልሉ ባለሙያዎች ከሐምሊን የካበተና የላቀ ክህሎት እንዲማሩም ማድረግ ተችሏል ሲሉም የቢሮው ኃላፊ ለዶ/ር ቢተው መስክረዋል፡፡



የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡


*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*


Hamlin Fistula Ethiopia


*Designed & printed by Everest printers*